# ሠ ቅ ጿ ል

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም ፲፫ | ቀን: መጋቢት ፮/፲ | በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ




## እስከ መቼ የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ መቀጠል ይቻላል?

የትግሬ ወያኔ ተፈጥሮአዊ ባሕሪው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የሆኑ አገሮች ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ የቆመ በመሆኑ ምክንያት፣ ሕዝቡ በተለምዶ አጠራር "በባንዳነት" የፈረጀዉ መሆኑ በሚገባ ይታወቃል:: ለዚህ ድምዳሜ የደረሰውም "ባንዳ" የአገሩን ነፃነት፣ብሔራዊ ሉዐላዊነትና ማንነት ለጠላት አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ ነዉ::

ባንዳነት የአገር ክሕደት ተግባር ነው። ይህ ተግባር ደግሞ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተከሰተ አሳፋሪና ወራዳ እንደሆነ በግልጽ ይታወቃል። ባንዳዎች ለነፃነትና ሉዐላዊነት የቆሙ የአገርና የማንነት ዘቦችን ሕይወት አደጋ ላይ የጣለና በዘመነ ቅኝ ገዥዎች በስፋት የተሰራበት በመሆኑ ብዙ ትንታኔ የሚሻ አይደለም:: ለአብነት ያህል የደቡብ አፍሪካ የትቂት መጤ ነጮች ዘረኛ አስተዳድር ያለ አገሬዉ ጥቁር ኅምቱ ባንዳዎች ትብብር ያን ያህል ዘመን በደቡብ አፍሪካ ተንሰራፍቶ ለመኖር ባልቻለ ነበር። በቬትናም የሆነዉም በተመሳሳይ ሁኔታ መጀመሪያም በፈረንሳዮች በኋላም በአሜሪካኖች በፖለሲ ደረጃ በስፋት የተሰራበት ስልት "አገር ወዳዱንና ለነፃነት የሚዋደቀዉን ቬትናማዊ ጀግና በባንዳ ቬትናማዊ ማስገደል" ነበር::

እርግጥ ነዉ የትግሬ ወያኔን ሁኔታ ከላይ ለማሳየት ከመከርነዉ እጅግ በጣም የተለየ የሚያደርገዉ፣ ወያኔ አንድም ጊዜ እንኳ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ስለማያምን ሁሌም የሚንቀሳቀሰዉ ሁለት ተደጋጋፊ እቅዶችን ጎን ለጎን አዝሎ በመሄድ ነዉ:: እነሱም ኢትዮጵያዊ መስሎ ለመሄድ በሞከረባቸዉ 27 ዓመታት የባንዳነት ተግባሩ ዉስጥ ሁሌም ራሱን የጥቁር አፓርታድ ሥርዓት መሪ ሆኖ፣ ቢችል ኢትዮጵያን ጥገት ላም አድርጎ በማለብ፣ የዚህ ዓላማው ተቀናቃኝ ይሆነኛል ያለውን ወገን ሁሉ በተለይም ዐማራውን እያጠፋ መኖር ታላቁ ሕልሙ ነው። በዚህ መቀጠል የማያስችለው ሁኔታ ሲፈጠር ደግሞ የግሌ የሚላትን ትግራይን ከሌላዉ የኢትዮጵያ ግዛት ገንጥሎ በመዉሰድ ሉዐላዊ አገር በመመሥረት ላይ የሚያጠነጥን መሆኑ ነዉ::

# እስከ መቼ የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ መቀጠል ይቻላል?

ይህም በመሆኑ የትግሬ ወያኔ ከላይ ለማመላከት የሞከርናቸዉ ሁለቱን መርሐ-ግብሮቹን ጎን ለጎን ደጋግፎ ለማስፈፀም እንዲያመቸዉ በማቀድ እንደ ጭቃ ጠፍጥፎ በጉዳይ አስፈጣሚነት የሠራቸዉ የባንዳ ተላላኪ የጎሳ ሊሂቃንን (ሆዳሞች እየተባሉ የሚጠሩትን) በመጠቀም ኢሕአዴግ የሚል ጭምብል በማልበስ መጠቀሙ ግልጽ ነው ። ሆኖም ግን፣ ላለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ይህ የወያኔ ጭምብል ጎንደር ላይ በተስተጋባዉ ፋና ወጊ መፈክር ምክንያት፣ ጭራሽ እርቃኑን ቀርቶበት ወያኔ ሲሻዉ ኮማንድ ፖስት አልያም ጊዜአዊ ወታደራዊ አዋጅ አዉጆ ሕዝባችንን በይፋና ከባለፈዉ በከፋ መልኩ እየገደለ እንደሚገኝ በሞያሌ፣ ጎንደር፣ ጎጃምና ሸዋ ሰሞኑን በግፍ የገደላቸው ዜጎች ደም ለዓለም ማኅበረሰብ ድምፅ እያሰማ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነዉ።

ለዚህ ደግሞ ራሱ የትግሬ ወያኔ «በባለ ዕራዕዩ» መሪዉ መለስ ዜናዊ መመሪያ "ክልሉም ያንሳል፣ ቁጥሩም ይቀንሳል!" መፈክር መሠረት፣ ዐማዉን በገፍ ለመግደልና "የነገዱ ቁጥሩም ከብዙኃንነት ወደ ዉሑዳን መለወጥ ይችላል" ብሎ ባለዉ የቆየ ፖሊሲ መሠረት በጎንደር፣ በጎጃም፣ በሸዋ፣ ወሎ ለልጆቹና ለንብረቱ መጠበቂያ ብሎ ዐማራዉ የገዛዉን የነፍስ ወከፍ መሣሪያ በአዲስ ዙርና ስልት ለማስፈታት የአካባቢ ተወላጆችን ለዚሁ ተግባር አሰልጥኖ በማሰማራት ነዋሪዉን እርስ በእርሱ ደም እያቃባና እያጋደለ ያለ መሆኑ መረጃዎች በስፋት እያሳዩ ነው።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ፣ አገር ያወቀዉንና ፀሓይ የሞቀዉን የትግሬ ወያኔን የባንዳነት ተግባር አሁን እንደ አዲስ በመጨረሻዉ ምዕራፍ ለመናገር ታስቦ ሳይሆን፣ ሕጋዊነት የሌለዉን የጊዜአዊ አዋጁን ተከትሎ የኢጋዚ ጦር በመላ ኢትዮጵያውያን በተለይም በኦሮሞ እና ዐማራ ነገዶች ላይ ያነጣጠረ ትጥቅ የማስፈታት ዓላማ አያሌ ባንዳዎች የጉዳዩ ተባባሪ በመሆን በወገናቸው ላይ እጅግ በጣም አሳሳቢ የሆነ የሕዝብ ዕልቂት እየተፈጸመ ያለ በመሆኑ፣ የሚመለከታቸዉ ዓለም አቀፍ፣ አሕጉር አቀፍና ከሁሉም በላይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁኔታውን አጢነው አስፈላጊውን የመከላከል እርምጃ እንዲወስዱ ከወዲሁ አቅጣጫ ማሳየትና ሊወስዱ ስለሚገባዉ ጥንቃቄ ለማስገንዘብ ነው።

የትግሬ ወያኔ መላ ኢትዮጵያን መዉረር የቻለዉ በወቅቱ የነበረዉን የኃይል አሰላለፍና የዓለም የፖለቲካ ሁኔታ መለዋወጥ የፈጠረዉን ክፍተት በመጠቀምና የአገራቸዉንና የራሳቸዉን ወገንና ነገድ ክብርና ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ በሰጡ በመንገድ መሪዎችና ከሐዲዎች ብርቱ እገዛ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል።

ሆኖም ግን፣ ይህ አስነዋሪ ክሕደት የትግሬ ወያኔ ኢጋዚ ቅልብ ጦር ራሱ በቀጥታ እየፈጸመ ካለዉ ግድያና ዘረፋ እጅግ በጣም የከፋ፣ አሳፋሪና በወገናችን ጭራሽ ይቅር የማይበል ነዉና፣ ይህ የተላላኪነትና የትግሬ ወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚነት ተግባር ላይ የተሰማራችሁ የዐማራ ነገድ ተወላጆች ሁሉ፣ ከዚህ አሳፋሪ ድርጊታቸዉ እጃቸውን በአስቸኳይ እንዲያነሱ ይጠየቃሉ። ለዚህ ጥሪ ተገቢውን አዎንታዊ ምላሽ ካልሰጡ ሕዝቡ ሊወስደው የሚችለው እርምጃ ትውልድ ተሻጋሪ ሊሆን እንደሚችል ሊያቁት ይገባል።

# እስከ መቼ የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ መቀጠል ይቻላል?

በተለይም ዐማራዉ በባህሉና ታሪኩ ልጆቹንና ንብረቱን የሚጠብቅበት የነፍስ ወከፍ መሳሪያዉን ለማስፈታት በወያኔ ስልጠና ተሰጧቸሁ ዐማራዉን ትጥቅ ለማስፈታትና እርስ በእርስ ለማጋደልና ሊደርቅ ወደ ማይችል ደም እያቃባቸዉና እያገዳደላችሁ ያለና የወያኔን ግልጽና ሥዉር ሤራ በጉዳይ አስፈጻሚነት እያገለገላችሁ ያላቸዉ የዐማራ ነገድ ተወላጆችና ሌሎችም ሁሉ ከዚህ መሰሉ አሳፋሪና ነዉርኛ ድርጊታችሁ ዛሬዉኑ እጃችሁን አንሱ። እንዲያዉም በእጃቸዉ ያለዉን መሳሪያ ወደ ታሪካዊ ጠላታችን ባንዳ የትግሬ ወያኔ የምታዞሩበት ቀን ቢኖር ነገ ሳይሆን አሁኑኑ መሆኑን ተገንዘቡ። ይህን ሳታደርጉ ብትቀሩ በሂደት ታሪክ፣ ትዉልድና የራሳችሁ ሕሊና ጭምር ወደ ፊት የሚወቅሳቸዉ መሆኑን እወቁ! ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን የጨለመዉ ጊዜ መንጋቱ አይቀርምና ያኔ ከተጠያቂነት አታመልጡም --- ከሕዝብ ዐይን ማምለጥ አይቻልምና!! የጀግናው ጎቤ መልኬ፣ የመቶ አለቃ ደርቤ አየለና የሌሎችም የጀግንነት ዉሎ ነገ በታሪክ ሲወሳ፣ በጉዳይ አስፈፃሚነት ቆመው የጠላትተባባሪ የሆኑም ከሕዝብ ዐይንና ሕሊና መደበቅ አይችሉምና ለፍርድ የሚቀርቡበት ቀን እሩቅ አይሆንም!!

ኩሩዉና የጀግናዉ ልጅ የዐማራ ነገድ ተወላጅና የዐማራ ነገድ ወዳጅና የትግል አጋር የሆንህ ሁሉ ዛሬ የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ላንተና ወዳጆችህ እጅግ በጣም ታላቅ ክብርና አድናቆት እንዳለዉ ስንገልጽ በታላቅ አክብሮት ነው። በትግሬ ወያኔ አጋዚ ታጣቂ በጉዳይ አስፈጻሚነት የተሰለፋችሁ ወገኖች በሕዝባችን ላይ እየተፈጸመበት ያለውን ግፍና መካራ የቱን ያህል የከፋ እንደሆነ ዐኅኢአድ በሚገባ ይገነዘባል። በዚያ ቀዉጢ የአርበኝነት ዘመን ጀግኖቹና አርበኞቹ አባቶቻችን ባንዳን ምን ያህል በጽኑ ይጠሉና ይጠየፉ እንደነበር ታሪካቸው ያሳያል። ዛሬ የትግሬ-ወያኔ ሕዝባችን ትጥቅ ለማስፈታትና በምትኖርበት ሕብረሰተብ ዉስጥ ያለ አባቶችህ ልምድና ባሕል የሀፍረት ካባ ሊያከናንቡህ የሚሞክሩትን የትግሬ ወያኔ ተላላኪዎች ትጥቅ አስፈች ሰልጣኞች ላይ የማያዳግም ትምህርት በመስጠት የታቀደልህን ዕልቂት ወደ ጠላቶችህ እንድታዞር ወኔህን አዘጋጅ። ሁኔታዉና መንገዱ ካለህ ከዚህ መሰል ነዉረኛ ድርጊታቸዉ አርፈዉ እንዲቀመጡ በዘመድና በሚመቸዉ መንገድ ሁሉ ማንነትህን ሳታሳዉቅ አሳዉቃቸዉ። ይህን ማድረግ የምትችልበት ሁኔታ ከሌለ ግን ለነዚህ መሰል ተላላኪዎች ምሕረት አይኑርህ። ለልጆችህና ለንብረትህ መጠበቂያ ብለህ የለሌ ጥሪትህን አፍስሰህ የገዛህዉን የእጅ መሣሪያህን ግን ለማንም እንዳትሰጥ። ይልቁንስ በአንተ ላይ ያንጃበበዉን አደጋ በብቃት ለመመከት ከመስል ወገኖችህ ጋር የጋር ስልትና እቅድ እያወጣህና እርስ በእርስህ እየተጠባበቅህ ይህን የትግሬ ወያኔ ክፉ ዘመን በአሸናፊነት ለመወጣት በቁርጠኝነት ቁም!። የጀግና ሰዉ ሞቱ ክብሩ ነዉና!!

የዐማራዉ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ተንሣኤ ነዉ!!

ድል ለዐማራዉ!!